# |ካንጋሮ ነው ´የተባለው ፍ/ቤት ክራሞት

ዮናስ 12/31/13

ፖለቲካና ፖለቲካዊ ወግ በዚህች አገር ላይ መቼም ምርጫ 97ን ተከትሎ የናኘውን ያህል በእኛ እድሜ አይተንም ሆነ ሰምተን የምናውቅ አይመስለኝም። በተለይ ገዢውን ፓርቲ በጥላቻ ፖለቲካ ለማጥቃት ያበረው ስብስብ አየሩን ባልተለመደ የፖለቲካ ጢስ ያጠነበት ያ ወቅት መቼም የሚዘነጋ አይደለም። በተለይ በምርጫው ዋዜማ ፖለቲካን በማያውቁ ወገኖች ላይ ሲወራጩ እና ሲፈነጩ የነበሩ የተቃዋሚ ሃይሎች ያሳደሩት አሉታዊ ተጽእኖም በቀላሉ አይረሳም። በፖለቲካውም ሆነ በፖለቲካ አመራር ጥርሳቸውን የነቀሉት የገዢ ስርዓቱ አመራሮች በወቅቱ የነበረውን መወራጨት ተገቢነት እንደሌለውና ለአገርም፣ ለእርሱም፣ ለእነርሱም እንዲሁም ባጠቃላይ ለማንም እንደማይበጅ በተለይ በከተሞች አካባቢ ሲሰጡ የነበረው ምክር የሚሰማ ጆሮ የመጥፋቱም ጉዳይ ሌላው የማይረሳው አሳዛኝ የምርጫ 97 ትዝታችን ነው።

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ካለው መልካም ስብእና አንፃርና ህገመንግስታዊ ስርዓቱ ለቀለም አብዮት የተመቸ ቀዳዳ የሌለው መሆኑ በጀን እንጂ የታሰበውማ ሌላ እንደነበር የገባንም እያደር ነው። ምንና ምን እያደር ይቀላል እንዲሉ አያቶቼ ያ በዋዜማው የነበረው ወጀብ፣ ያ በወቅቱ የነበረው የከበደ አየር ከምርጫው ማግስት ላይ በዛው ፍጥነት መተንፈሱን እና መደፍረሱን ሲያያዘው ሁሉም ነገር ግልጽ እየሆነና በህዝብ ዘንድ መረዳትን እያገኘ መጣ። መረዳቱም ያ የተባበረው የጥላቻ ፖለቲካ ክንድ ሳጋና ማገር የሌለው ጎጆ እንደሆነ፤ በአናቱም ምርጊቱም ጭድ አልባና በደንብ ተገላብጦ ባልተቦካ ጭቃ የተከናወነ እንደሆነ በአደባባይ መጋለጥ ጀመረ። በጠላቴ ጠላት የተሰበሰበው ሃይል ቢያንስ ከማያውቁት መላክ የሚያውቁት ሴጣን ይሻላልን ብሂል በመዘንጋት ለየቅል የሆነውን ርዕዮተ ዓለም ይዞ አሻፈረኝ ቢልም የጠላቴ ጠላት ስለፖለቲካ ግማሽ መንገድ እንኳ እነደማያሻግር የተረጋገጠው

ወዲያውኑ እንደነበር ሁኔታውን ቅርብ ስንከታተል የነበርን ሰዎች መቸም አንዘነጋውም።

ያ |የተባበረ የጥላቻ ፖለቲካ ክንድ´ ዘይትና ውሃ ሆኖ እምቢኝ ሲል፤ ያ ወደሌላ አቅጣጫ ሲወረወር የነበረ ድንጋይ ተመልሶ ወርዋሪውን ሲፈነክት (boomerang)፤ ያ ወደሌላ ያነጣጠረና የተቀሰረ ጣት ወደርሱና ተመልሶ እርስ በራሱ ላይ ሲጠቋቆም፤ ያ አንተ ትብስ ወደ እኔ እበልጥ ሲቀየር፤ ያ በሰው ንዳድ ሲሞቅ የነበረ ሃይል እርስ በርሱ እሳት ሲወራወር፤ አቋራጩ መንገድ ተሳክቶ ቢሆን ኖሮ "ምን ያደርጉን ነበር" ያለለ ሰው እንደሌለ የማይዘነጋና ሌላው ትዝታችን ነው ። እኛ "ምን ሊያደርጉን ነበር?" ብለን ብቻ ብናበቃም የሚመለከተው አካል ለጠፋው ጥፋትና ለወደመው ንበረት ተጠያቂ ሃይሎችን በህግ አግባብ ሲቆጣጠር ደግሞ ያልወጣለት ስምና ስያሜ አንዳልነበረም አንዘነጋም።

በወቅቱ እሳቱን ሲሞቁና ሌላውን ሲማግዱ የነበሩት እነዚህ ሃይሎች ሲያዙ በስርዓቱ እና መንግስት ላይ ለከፈቱት መሰረት የለሽ ስም ማጥፋት ዘመቻ ያፍሩ ዘንድ ጊዜ አልወሰደባቸውም። ህገ መንግስቱ ባጎናፀፋቸው ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት በመጠቀም በየሚዲያው ላይ ጦር ሲወረውሩበትና ሲዘላለፉበት የከረሙት፣ ያለማገርና ሳጋ የተጠላለፉት ስብስቦች እንኳንስ በትልቂቱ ኢትዮጵያ ይቅርና በትንሽ አጥር ግቢ (ማረሚያ ቤት) ውስጥ ሲገናኙ እራሳቸውን ሊመረምሩና ሊፈትሹ ቀርቶ የተገኙት የተፋፋመ የርስ በርስ ተኩስ ውስጥ ነው።

ከደጅ ሆነን ልንለየውና ምርጫ 97ን በፖለቲካ መነጽር ለመመልከት ለታደልነው ዜጎች እነዚህ ኃይሎች ስለጥፋታቸው ሌላ ምስክር የሚያሻቸው ስላለመሆኑና እርስ በእርሳቸው የተወራወሯቸው ድንጋዮች ብቻ በራሳቸው የአቃቤ ህግ ምስክሮች ሊሆኑ እንደሚችሉ ቢገባንም፤ ህግ የማስከበር ግዴታ ያለበት መንግስት ስለህገመንግስቱና ስለ ህግ የበላይነት ለመሰረተው ክስ ካፊርኩ አይመልሰኝ ስብስቦች ዳግም ሌላ ስምና ስያሜ ማውጣታቸውም አይረሳም።

በቃልቲ ማረሚያ ቤት እርስ በእርስ መወነጃጀልን እና መፈነካከትን ቁርስ፣ ምሳና እራታቸው ያደረጉት እነዚህ ሃይሎች ምስክር ሳያሻቸው አየሩን በጥላቻ ፖለቲካ ማጠናቸውና ጦስ ጥንቡሳሱም በደም ለተቋጨው መንገዳቸው ሊያስከስሳቸው የሚችል መረጃ ቢኖርም በህግ አግባብ ለቆሙት ምስክሮች የካድሬነት ስያሜ ሲያወጡ ለአቃቢያነ ህጎቹ የተላላኪነትን ካባ አጎናጽፈዋል። ከሁሉም የሚገርመው ደግሞ ለአራዳና ጭስ የሚሆነው መውጪያ ለዜሮ ድምር ፖለቲካ አይስማማምና አማራጭ ያደረጉት አምነውበት ለገቡበትና ሲያለሙም ሲያጠፉም ሊዳኙበት ቃል ኪዳናቸውን ላኖሩበት ህገመንግስቱና ፍርድ ቤቱ ታፔላ መለጠፋቸው ነው። ለፍርድ ቤቱን ‘የካንጋሮ ፍርድ ቤት’ የሚል ስያሜ ሲሰጡት ለህገመንግስቱ ደግሞ ‘ህገ አራዊት’ የሚል ህዝብና መንግስትን ያላገናዘበና ያልተረዳ ታፔላ ለጠፉለት።

ይሁን እንጂ እነዚህ በካፈርኩ አይመልሰኝ ሱስ የተጠመዱት ሃይሎች ‘የካንጋሮ ፍርድ ቤት’ ባሉት ችሎትና "ህገ አራዊት" ባሉት ህገ መንግስት ፊት ስንት ጊዜ ነፃ እንደወጡ እና ስንት ጊዜም ከፊት ቆመው እንደተሟገቱ ለምናውቀው ዜጎች ምን ያህል እየወረዱና እየባሰባቸው እንደመጣ ለመገንዘብ አይከብደንም። ጥቂቶቹን እንኳ ብናስታውስ እነዚህ ኃይሎች የተዳኙትና ጥፋተኛ ሆነው የተገኙት በህገ መንግስታዊ ስርዓቱ አግባብነት በችሎት ፊት ቆመው፤ ጠበቃም አቁመውና ቆሞላቸው ባደረጉት ክርክር ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸውና ጥፋተኛ አለመሆናቸውን የሚያረጋግጥ መከላከያ ማቅረብ ባለመቻላቸው ነው።

በእርግጥ በመከላከያ እጦትና በሌሎችም ተያያዥ ምክንያቶች ተከሳሹ ከሳሽ፣ ጥፋተኛው ነፃ፣ ነፃው ጥፋተኛ ሆኖ የሚገኝበትም አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ቢታወቅም ጥፋተኛም ሆኖ የተፈረደበት መማረሩ፤ በውሸትም ክስ የተፈረደለት ማመስገኑ የተለመደና ክፉ ልማድ የሆነበት ዘመን ላይ መሆናችን ይታወቃል። ያም ሆኖ ግን እነዚህ ሃይሎች ከወጡም በኋላ እርስ በእርስ ከተወራወሩት ጠጠርና ከተፈነካከቱባቸው መፃህፍቶች መረዳት የሚቻለው በእርግጥም ጥፋተኛ ስለመሆናቸውና በህግ የበላይነት ፊት ቆመው በመዳኘት የቀረበባቸው ውሳኔ ትክክል እንደነበር ነው።

ሌላውን ስናነሳ ደግሞ እነዚህ ኃይሎች ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበትን ችሎት የ"ካንጋሮ ፍርድ ቤት" ቢሉትም፣ ህገመንግስታዊ ስርዓቱን "ህገ አራዊት" ቢያደርጉትም። "ከተፃፈበትም እስክሪፕቶ እና ወረቀት ያልተሻለ" ሲሉ ቢዘባበቱበትም በእርሱው አገባብ ይቅርታ መጠየቃቸውንና በእርሱ አግባብ ስለመድበለ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና ጤናማ የፖለቲካ አየር ሲባል በወንጀላቸው ምክንያት ከተቀፈደዱበት ወርኅ መላቀቃቸውም ይታወሳል። የተቀሩት ፍንክትካቾች በምርጫ 2002 ሊሳተፉ ተመዝግበው ሳለ ፊሽካ ሳይነፋ ቀድመው ያን ለይቅርታ ያበቃቸውን ህገ መንግስትና ለምርጫው መሰረት ያደረጉትን የህግ የበላይነት እስኪያቅራቸው ዘለዘሉ። ምን ይህ ብቻ ሳይጀመር ተጭበርብሯል ሲሉ የቆሙትም እዛው "የካነጋሮ . . . " ባሉት ፍርድ ቤት ነው። እርስ በርስ "መርህ ይከበር" ሲሉና በጥላቻ ፖለቲካ ሲታመሱም ክሳቸውን ይዘው አቤት ያሉት እዛው *የካነጋሮ . . .* ባሉት ፍርድ ቤት ". . . ህገ አራዊት" የሚሉት ህገ መንግስታዊ መብታችን ተጥሷል ሲሉ ነው። በማህተም ሲቧቀሱ፣ በማእከላዊ ኮሚቴ ምርጫ ሲላተሙ፣ በአቅም ማነስና በአንጃነት ሲፈራረጁና ሲጠፋጠፉ፣ በመዋሃድና ባለመዋሃድ፣ ግንባር በመፍጠርና ባለመፍጠር መሃል ላይ ሆነው በልዩነት ሲታመሱ፣ ልዩነታቸውን በዘለፋ እና ስም በማጥፋት ዘመቻ በየጋዜጣው ላይ ሲያወራርዱ፣ ምህዳር ጠበበኝ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ተከለከልኩ፣ ሲሉ ብቻ እርስ በእርሳቸው አንዱ በዳይ፣ ሌላው ተበዳይ እየሆኑ ሲጮሁና ሲጯጯሁ፣ ህገደንብ ሲያረቁ በሚፈጠሩ ልዩነቶችና፣ በጠቅላላ ጉባኤ ላይ ከመጋረጃ በስተጀርባ የፖለቲካ ደባዎች ተፈጥረዋል ሲሉ ከየትም ይሁን ከየት፣ ከየትም ይምጣ ከየት ተበደልን ባሉ ጊዜ ሁሉንም ያየናቸው እዛው "የካንጋሮ ፍርድ ቤት" ሲሉ በሰየሙት ችሎት ፊት ነው። የክሳቸው መጀመሪያም ያው "ህገ አራዊት" ያሉትን ህገ መንግስት መሰረት ያደረገ ነው። ለዘለፋና ስድባቸውም ከለላዬ ሲሉ የሚጠቅሱት ያንኑ "ህገ አራዊት" ያሉትን ታላቅ ሰነድ እንደሆነም እናውቃለን።

ከላይ ከዘረዘርናቸው በተጨማሪ ሌላው ጥሩ ማሳያና ማረጋገጫ የሚሆነን ጉዳይ እሩቅ ሳንሄድ መንግስት በአክራሪነት ላይ ከከፈተው ዘመቻና እርምጃ ጋር ተያይዞ የ"ካንጋሮ ፍርድ ቤት" እና የ"ህገ አራዊት" ስም ሰያሚዎችና አቀንቃኞች መሃረነ ክርስቶስ ያሉት "ከተፃፈበትም ወረቀትና እስክሪፕቶም የላቀ ጠቀሜታ የሌለው ነው"

ባሉት ህገ መንግስትና የህግ የበላይነት መሰረት ላይ ቆመው መሆኑ ነው። ከዚህ ትውስታችን መገንዘብ የሚቻለው ህግ አስከባሪውም ሆነ ከአክራሪነት ጋር ጋብቻ ፈጽሟል የተባለው ሃይል የሙግታቸው ማእከል ህገመንግስቱና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱ መሆኑን ነው።

ህግ የማስከበር ህገ መንግስታዊ ሃላፊነት አለብኝ የሚለውም መንግስትና ስለአክራሪነትና ከአክራሪነት ጋር ተያይዞ ተሰርቷል ለሚላቸው ወንጀሎች የሚያቀርባቸው መከራከሪያዎች መነሻው ህገ መንግስትና የህግ የበላይነትን የተመለከቱ አስረጂዎች ሲሆኑ፤ ከአክራሪነት ጋር ጋብቻ ፈጽሟል የተባለው ሃይልና ተሳትፏል የተባለው ተጠርጣሪ ከላይ ለቀረበው ክስ መከራከሪያዬ ነው ሲል የሚያቀረባቸው አስረጂዎችም በተመሳሳይ ህገ መንግስቱን መሰረት ያደረጉ ናቸው። ልዩነታቸው ህገመንግስቱን የማክበርና የማስከበር እና ህገመንግስታዊ ስርአቱን በሃይል የመናድና የማስናድ ጉዳይ ነው። ሌላው ልዩነት፣ ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም እንዲሉ መረጃና ማስረጃው ባጠራቸው ጊዜ ከለላችን ነው ያሉትን ህገ መንግስትና አምነውት የቆሙበትን ችሎት መልሰው "የካንጋሮ ፍርድ ቤት" ሲሉ መሰየማቸው ስለመሆኑ ከላይ የተመለከተው ትውስታችን ዋቢ ይሆነናል።

ችግሩ *የገዢው ስርዓት ጉዳይ አስፈፃሚ* ሲሉት የነበረው ፍርድ ቤት፤ *ለገዢ ስርዓቱ የስልጣን ማራዘሚያ ኪኒን* ሲሉ የዘለፉት ህገ መንግስት፤ ዜጎች ሁሉ በህግ ፊት እኩል እንደሆኑ እና ህገመንግስታዊ ስርዓቱ የሁሉም እንደሆነ የሚያረጋግጥ እውነት ሰሞኑን በዚሁ ፍርድ ቤት መከሰቱ ብዙዎቻችንን ቢያስደምም *እነዚህ ሃይሎች ምን ነካቸው? ምንስ ይሻላቸዋል?* እንድንል ያስገደዱን እና እምን አይነት ጥፍር ውስጥ እንደሚደበቁም ለማወቅ የናፈቀን ሆኖ አግኝተነዋል።

ይህም ክስተት ከምርጫ 97 ዋዜማ ጀምሮ የተለየ ታፔላ ሲለጥፉባቸው የነበሩ ፍርድ ቤቶችና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ነፃና የሁሉም ስለመሆናቸው ከላይ በተመለከተው አጭር ዳሰሳ የቀረበ ቢሆንም ከአክራሪነት ጋር ተያይዞ ከቀረበው የቅርብ ትውስታችን አንፃር ፍርድ ቤቱም ነፃ ስለመሆኑና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱም የሁሉም መሆናቸውን ያረጋገጡበት ተጨባጭ ክስተት ነው።

አክራሪ ሃይሎችም ሆኑ ከአክራሪነት ጋር ጋብቻ የፈፀሙ ሃይሎች ህገ መንግስቱን እና የህግ የበላይነትን ከለላ አድርገው በአንድ ወገን እየተሟገቱ፤ በሌላ ወገን ደግሞ ችሎቱን ሲያቀሉ እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ለማንኳሰስ ሲሞክሩ ቢቆዩም በአወልያ ትምህርት ቤት ከተፈጠረው አለመግባባት ጋር ተያይዞ በ28 ሰዎች ላይ የቀረበውን የሽብር ክስ ሲያዳምጥ የከረመው "የካንጋሮ ፍርድ ቤት (በእነሱ አጠራር)" ታህሳስ 3/2006 ዓ.ም በሰየመው ችሎት የአቶ ጁነዲን ሳዶን ባለቤት ጨምሮ 10 ተከሳሾችን በነፃ በማሰናበትና 18 ተከሳሾች ደግሞ መከላከያ እንዲያቀርቡ በሰጠው ብያኔ ፍርድ ቤቱ ነፃ መሆኑን ብቻ ሳይሆን መላው ዜጋ በህግና ህገመንግስታዊ ስርዓቱ ላይ እምነት እንዲኖረው ማድረግ ችሏል፤ የ"ካንጋሮ ፍርድ ቤት" ሰያሚዎችን እና አራጋቢዎቻቸውንም ፀጥ አሰኝቷል ብቻ ሳይሆን ኩምሽሽም አድርጓል።

ፍርድ ቤቱን እንደማያምኑት፣ ህገ መንግስታዊ ስርዓቱም ለገዢው ሰርዓት እንጂ ለዜጎች እንዳልሆነ በተደጋጋሚ ሲናገሩ እና በየፕሬሱ ላይ ሲያብጠለጥሉት የምናውቃቸው የተከሳሾቹ ጠበቃ አቶ ተማም አባቡልጉ፤ ያ አናምነውም ያሉትና ይልቁንም የካንጋሮ ፍርድ ቤትነቱ ያመዝንብናል ያሉት ፍርድ ቤት የሽብር ድርጊት ፈጽመዋል ተብለው ተከሰው የነበሩት ደንበኞቻቸው የሽብር ድርጊት ስለመፈፀማቸው የሚያስረዳ ነገር ፍርድ ቤቱ ባለማግኘቱ በነፃ ያሰናበታቸው እንደሆነና፤ ተከላከሉ የተባሉትም ቢሆን የሽብር ድርጊት መፈፀማቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ፍ/ቤቱ ባለማግኘቱ የሽብር ድርጊትን በማነሳሳት ስር ተከላከሉ የሚል ብይን እንደሰጠ ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ሲናገሩ ሰምተናል። ደንበኞቻቸው የሽብር ተግባር ፈፀሙ፣ አልፈፀሙ፤ መንግስት ፈጽመዋል ሲል ከሰሰ አልከሰሰ፤ እውነታው የህሊና ጉዳይ ሆኖ ዋናው ነገር ፍ/ቤቱ በቀረበለት ማስረጃና የመከራከሪያ አጀንዳ ላይ ብቻ ተመስርቶ ውሳኔ የመስጠት ሃላፊነቱን መወጣት የሚያስችል ነፃነት እንዳለው ያረጋገጥንበትና የ"ካንጋሮው ፍ/ቤት"ን ሰያሚዎች የሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ጉዞ በተጨባጭ ለመንቃት ያስቻለን ዓቢይ ጉዳይ ነው።

በመጨረሻም፣ ስለህግ የበላይነት እንኖራለን፤ ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ጠብቀን እና አክብረንም በእርሱ ምድራዊ ህይወታችንን እንገፋለን።